# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 281 መስከረም 17 2005 ገጽ 1

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

**የግንቦት ሰባት ንቅናቄም ይህን የጀግና ውስኔ የወሰኑ እነዚህን አራት የአየር ሃይል አብራሪዎችና አስልጣኝ መኮንኖች እንኳን ተወለዳችሁ፤ እንኳንም ተማራችሁ፤ እንኳንም ወደ ነፃነቱ ትግል ተቀላቀላችሁ እያለ ደስታውንና ለጀግኖቹ ያለዉን ከፍተኛ አክብሮት ይገልፃል። ውሳኔያችሁ ከፈርዖን ቤተ-መንግስት ምቾት ይልቅ ከህዝቤ ጋር መሰደደ ይሻለኛል ያለውን የታላቁን ሰው የሙሴን ውሳኔ ይመስላልና የወሰዳችሁትን ትክክለኛ እርምጃ ትውልድ ምን ግዜም አይረሳዉም።**

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## ግንቦት 7 ዋሽንግተን ዲሲ ዉስጥ ትልቅና የተሳካ ህዝባዊ ስብሰባ አካሄደ

ግንቦት 7 የፍትህ፤ የነጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ባለፈዉ እሁድ መስከረም 13 ቀን 2006 ዓም አሜሪካዋ መናገሻ ከተማ ዋሽንግተን ዲሲ ዉስጥ ስብሰባ አካሂዶ በተለያዩ ህዝባዊ ትግሉንና ንቅናቄዉን በተመለከቱ ጉዳዮች ዲሲ፤ ሜሪላንድና ቨርጂኒያ ዉስጥ ከሚኖሩ አያሌ ኢትዮጵያዉያን ጋር ሲመክር መዋሉን ዋሽንግተን ዉስጥ የሚገኙ የንቅናቄዉ ቃል አቀባዮች ተናገሩ። በዚህ የንቅናቄዉ ሊ/መንብር ዶ/ር ብርሀኑ ነጋ፤ ዋና ጸሀፊዉ አቶ አንድአርጋቸዉ ጽጌና የህዝብ ግኑኝነት ዘርፍ ሀላፊዉ አቶ ኤፍሬም ማዴቦ በተገኙበት ስብሰባ ላይ ጋ ጥሪ የተደገላቸዉ አንግዶች፤ ዜጠኞችና የተለያዩ ፓርቲና ሲቪክ ድርጅት መሪዎችና ተወካዮች የተገኙ ሲሆን አቶ አንዳርአቸዉ ጽጌና ዶ/ር ብርሐኑ ነጋ ከህዝብ ለቀረበላቸዉ በርካታ ጥያቄዎች አጥጋቢ መልስ ሰጥተዋል። የዕለቱን ስብሰባ በተላያዩ የፓልቶክ መወያያ መድረኮች ቁጥሩ ከ3500 በላይ የሆነ ሰዉ የተከታተለዉ ሲሆን አቶ አንዳርጋቸዉ ጽጌና ዶ/ር ብርሀኑ ነጋ ከፓል ቶክ ለቀረበላቸዉ ጥያቁም መልስ ሲሰጡ ዉለዋል።

የእለቱን ስብሰባ የመሩት የንቅናቁዉ የህዝብ ግኑኝነት ዘርፍ ሃለፊ አቶ ኤፍሬም ማዴቦ ስብሰባዉን በንግግር ሲከፍቱ ባሰሙት ንግግር ግንቦት 7 ብዙ ግዜ ከተገንጣዮች ጋር ይደራደራል ተብሎ በተደጋጋሚ የሚነሳዉን ክስ አስመልክተዉ ሲናገሩ ከተገንጣይ ኃይሎች ጋር እንመክራለን እንደራደራለን፤ ለምን ቢባል እነሱም እንደማናችንም ኢትዮጵያዉያን ናቸዉ ብለን እናምናለን፤ ደግሞም ትናንት በጡንቻችን ተማምነን በኤርትራ ጉዳይ ላይ የሰራነዉን ስህተት መድገም አንፈልግም። የምናወራዉ ስለ አንድነታችን ከሆነ፤ የምናዉራዉ ስለሁሉን አቀፍ ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ከሆነ፤ የምናወራዉ ስለዘላቂ የአገራችን ሰላም ከሆነ መደራደርና መወያየት ያለብን ከወዳጆቻችን ጋር (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## የወያኔ ከፍተኛ ወታደራዊ መኮንኖች የደሞዝ ካልተጨመረልን ብለዉ አመረሩ

ከአንድ ወር በፊት የተጠናቀቀዉን የወያኔ ጀኔራሎች ስብሰባና የስብሰባዉን ዉሳኔ አስመልክቶ በመከላከያ ሠራዊቱ ዉስጥ በየቦታዉ በመካሄድ ላይ ያለዉ ከመቶ አለቃ በላይ ማእረግ ያላቸው ወታደራዊ መኮንኖች ስብሰባ ዋነኛዉ የመነጋገሪያ አጀንዳዉ የደሞዝ ጭማሪ ጥያቄ መሆኑ ታወቀ። አንድ ወር ቀደም ብሎ በተካሄደዉ የጄኔራሎቹ ስብሰባ ላይ ለሰራዊቱ የደሞዝ ጭማሪ የማድረግ ጥያቄ ተነስቶ የነበረ ቢሆንም፣ "ሰራዊቱ አሁን የሚያገኘው ደሞዝ ለኑሮው በቂ ነው" የሚል መልስ ከሰራዊቱ ዋና አዛዦች በመሰጠቱ ጥያቄዉ ዉድቅ መሆኑ የሚታወስ ነዉ። በወቅቱ የሠራዊቱን የደሞዝ ጭማሪ ጥያቄ ዉድቅ መሆን በመቃወም የወያኔዉ ጄኔራል ሰአረ መኮንን ስብሰባ ረግጦ እንደወጣ የሚታወስ ሲሆን በወቅቱ ጄኔራሉን ለማረጋጋት ከፍተኛ ጥረት ተደርጎ እንደነበር ይታወቃል።

ሰሞኑን በመካሄድ ላይ ባለው ከጄኔራል በታች ማእረግ ባላቸው መኮንኖች ስብሰባ ላይ እንደ ትልቅ የመነጋገሪያ አርዕስት ሆኖ የተወሰደዉ የደሞዝ ጭማሪና የኑሮ ውድነት ጥያቄዎቸ እንደሆኑ የሚታወቅ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ ዘራፊና ሙሰኛ በሆኑ የወያኔ ጄኔራሎችና ከጄኔራል በታች ባሉ መኮንኖች መካከል የሚታየዉ ከፍተኛ የኑሮ መበላለጥ ብዙዎቹን መኮንኖች ከማስቆጣቱም በላይ አንዳንድ መኮንኖች በድፍረት "እናንተ ሙሰኞች" እያሉ ሲናገሩ ተደምጠዋል። በምስራቅ አካባቢ ባለው እዝ አንዳንድ መኮንኖች " እኛ ቤተሰቦቻችንን ምግብ አብልተን ለማኖር አልቻልንም፣ እናንተ ግን የአገሪቱን ኃብት እየዘረፋችሁ በ ልጆቻችሁን ውጭ አገር ልካችሁ ታስተምራላችሁ" በሚል አለቆቻቸውን በድፍረት መተቸታቸውን የውስጥ ምንጮች ገልጸዋል። አንድ ስማቸዉ እንዳይጠቀስ የጠየቁ የስብሰባዉ ተሳታፊ እንደተናገሩት በስብሰባዉ ወቅት ከ መኮንኖቹ ይቀርብ የነበረዉን ጥያቄ የመደረክ መሪዎች መመለስ ተስኗቸዉ ሲደናበሩ ታይተዋል።

## ሚሚ ስብሃቱና አማረ አረጋዊ ወያኔ የሰጣቸዉን አደራ መወጣት አቃታቸዉ

በአፍቃሬ ወያኔነቷ የምትታወቀዉና ወያኔን ተከትላ ከዋሺንግተን ዲሲ አዲስ አበባ የገባቸዉ የምላስ እመቤቷ ሚሚ ስብሀቱ የኢትዮጵያን የመገናኛ ብዙሃን ምክር ቤት ወይንም ፕሬስ ካውንሰል ታቋቁማለች ተብሎ የተጣለባትን ወያኔያዊ አደራ መወጣት እንዳቃታት ታወቀ። ከወያኔ ጋር ባላቸዉ ንኪኪ የተነሳ በገዢዉ ፓርቲ ደጋፊነታቸዉ በሚታወቁት በሚሚ ስብሃቱ ሊ/መንበርነትና በአማረ አረጋዊ ምክትል ሊ/መንበርነተ የሚመራው ጊዜያዊ መስራች ኮምቴ ፕሬስ ካውንስሉን እንዲመሰረት ኃላፊነት ቢሰጠውም አመራሩ እርስ በርስ ባለመግባባቱና የብዙሃኑ ጋዜጠኞች አዎንታዊ ምላሽ ባለማግኘቱ የምስረታውን ጉዳይ የዉኃ ሽታ ሆኖ እንደቀረ ለማወቅ ተችሏል። ይህ በሚሚ ስብሀቱና በአማረ አረጋዊ መሪነት ስራዉን የጀመረዉ ኮሚቴ ሶስት አመታት ያስቆጠረ ቢሆንም በሁለቱ ዝናና ስም ናፋቂ ሰዎች መካከል በተፈጠረዉ ግልጽ የስልጣን ሽኩቻና መናናቅ ምክንያት ምስረታውን ማካሄድ እንዳልተቻለ ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው ምንጮች ጠቁመዋል፡፡

አሁን በስራ ላይ የሚገኘው የመገናኛ ብዙሃን ህግ በሚረቀቅበት ወቅት መንግስት የፕሬስ ካውንስል እንደሚያቋቁም ተደንግጎ የነበረ ቢሆንም በተለይ በግሉ ፕሬስ ያልተቆጠበ ተቃውሞ ረቂቅ ህጉ ተሻሽሎ እንዲወጣና በተሻሻለውም ሕግ መሰረት ፕሬስ ካውንስሉን የማቋቋሙ ኃላፊነት የሚዲያ ባለሙያዎች እንዲሆን መደረጉ ይታወሳል፡፡ የፕሬስ ካውንስሉ ቢቋቋም በተለይ ጋዜጠኞች በትንሽ በትልቁ ጉዳይ ፍ/ቤትና ፖሊስ ጣቢያዎች የሚመላለሱበትን በማስቀረት የሚቀርቡ ክሶችና ቅሬታዎች በአስተዳደራዊ መንገድ መፍትሔ ለማስገኘት ይረዳል ተብሎ ተስፋ ተጥሎበት ነበር፡፡ ከምርጫ 1997 በፊት 385 በላይ ጋዜጦችና መጽሔቶች የነበሩት በአሁኑ ወቅት እጅግ አሽቆልቁለው 16 ጋዜጦችና 17 መጽሔቶች ብቻ በህትመት ላይ ይገኛሉ፡፡ በአንጻሩ በመንግስት የተያዙ የራዲዮና የቴሌቪዝን ጣቢያዎች ቁጥር አድጎ በጠቅላላው 23 የደረሰ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ 15 ያህሉ የማህበረሰብ ራዲዮ ጣቢያዎች፣ ራዲዮ ፋናን ጨምሮ 5 የግል ራዲዮ ጣቢያዎች፣10 የመንግስት ጣቢያዎች 1 የቴሌቪዝንና፣ 3 የክልል ጣቢዎች ይገኙበታል።

## የወያኔዉ ደህንነት ከወልድያዉ የሙስሊም ተማሪዎች አመጽ ጀርባ ሼክ አላሙዲን አሉበት አለ

ወያኔ፤ ዘረኛ መሪዎቹና አጨብጫቢዎቹ በአልሻባብ፣ በአልቃይዳ ፣ በግንቦት ሰባትና በኤርትራ መንግስት ይደገፋል ከሚሉት የኢትዮጵያ ሙስሊሞች እንቅስቃሴ ጀርባ ቱጃሩ ነጋዴ ሼክ መሀመድ ሁሴን አላሙዲን ይገኙበታል ሲል የወያኔዉ የደህንነት መስሪያ ቤት ጥናታዊ መረጃዎችን ለአገዛዙ ከፍተኛ ባለስልጣኖች ማቅረቡ ታወቀ። በቅርቡ ወልድያ ከተማ ዉስጥ የከተማዉ ሙስሊም ተማሪዎች ባስነሱት አመጽ መንገድ ዘግተው ወደ ላሊበላ ፤ ሰቆጣ ፣ ደሴና አዲስ አበባ የሚደረጉ የትራንስፖርት ጉዞዎች እንዲስተጓጎሉ ማድረጋቸው የሚታወስ ሲሆን ከዚሁ ጋር በተያያዘ አመጹን አነሳስታችኋል የተባሉ 13 ታዳጊ ወጣቶችን አስረዉ የመረመሩት የደህነነት ኃይሎች አጣራነው ባሉት መረጃ አመጹን ሼክ አላሙዲን ከጀርባ ሆነው ደግፈውታል ሲሉ ተናግረዋል።

ኢሳት ዉስጥ አዋቂ ምንጮችን ጠቅሶ ባሰራጨዉ በዚህ ዜና የኢህአዴግ አመራርና የፌደራል ፖሊስ የጋራ የጸረ ሽብር ግብረ ኃይል በጉዳዩ ዙሪያ በሰፊው ውይይት ካደረጉበት በኃላ ፣ በባለሀብቱ ላይ እርምጃ ለመውሰድ ባይቻልም በወዳጆቻቸው በኩል ምክር እንዲሰጣቸው በአቶ በረከት ስምኦን የሚመራ አንድ ቡድን መዋቀሩን ለማወቅ ተችሏል። ይህንን በአገሪቱ ህግ መሰረት ከፍተኛ ቅጣት የሚያስቀጣ ወንጀል የፈጸመዉ ሌላ ሰዉ ቢሆን ኖሮ አንድ ቀንም ዉሎ አያድርም ነበር ያሉት አንድ ስማቸዉ እንዳይጠቀስ የጠየቁ ከፍተኛ የአገዛዙ ባለስልጣን ሼክ አላሙዲን ኢትዮጵያ ዉስጥ ያሰኘዉን ሁሉ መስራት የሚችል ሰዉ ነዉ ብለዋል። ሼክ አላሙዲን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከታክስ እና ከግንባታ ጋር በተያያዘ ከመንግስት ጋር ውዝግብ ውስጥ መግባታቸው ይታወቃል። የደህንነት መስሪያ ቤት በባለሀብቱ እንቅስቃሴ ዙሪያ መረጃ እንዳገኘ ቢገልጽም፣ መረጃውን እንዴት እንዳገኘው አልታወቀም። አንዳንድ ወገኖች ግን የሼክ አላሙዲን ከህግ በላይ መሆን ያሳሳበው መንግስት፣ አጋጣሚውን በመጠቀም ባለሀብቱን ለመምታት የፈጠረው ዘዴ ሊሆን ይችላል ይላሉ።

## እንደ ቆራጥ ንስር ፓይለቶቹ...

ባለፈው ሳምንት በኢትዮጵያውያን ዘንድ ዋና የመነጋገሪያ አርዕስት የነበረው አራት የአየር ሃይል አብራሪዎችና አስልጣኝ መኮንኖች ከዘረኞቹና ከዘራፊዎቹ ጎራ ወጥተው ወደ ነፃነት ታጋዮች ጎራ የመቀላቀላቸው ጉዳይ ነበር። እነዚህ ቆራጥና አገር ወዳድ አብራረዎች የወሰዱት እርምጃ ወገንን የሚያኮራና ከፍተኛ ጀግንነትን የሚጠይቅ ትልቅ ውሳኔ ነው። ይህ ውሳኔ ሰው ባጣች አገር፤ ጀግና ባጣች አገር፤ ለአገር ለወገን ተቆርቋሪ ባጣች አገር ውስጥ ትልቅ ተስፋ ሰጪ ነው። የኢትዮጵያ ህዝብ በያለበት በተለያየ መንገድ ይህን የጀግና ውሳኔ የወሰኑ ልጆቹን እያደነቀም እያመሰገነም ይገኛል።

የግንቦት ሰባት ንቅናቄም ይህን የጀግና ውስኔ የወሰኑ ወንድሞቹን እንኳን ተወለዳችሁ፤ እንኳንም ተማራችሁ፤ እንኳንም ወደ ነፃነቱ ትግል ተቀላቀላችሁ እያለ ደስታውንና ለጀግኖቹ ያለዉን ከፍተኛ አክብሮት ይገልፃል። ውሳኔያችሁ ከፈርዖን ቤተ-መንግስት ምቾት ይልቅ ከህዝቤ ጋር መሰደደ ይሻለኛል ያለውን የታላቁን ሰው የሙሴን ውሳኔ ይመስላልና የወሰዳችሁትን ትክክለኛ እርምጃ ትውልድ ምን ግዜም አይረሳዉም።

የእነዚህ ቆራጥ የኢትዮጵያ ህዝብ ልጆች፣ ሙያና ችሎታ ስጋዊ የሆነ ፍላጎታቸውን ለማርካት ከበቂ በላይ ነው። ከዘረኞቹና ከቃየላውያኑ ቡድኖች ጋር እየተሞዳሞዱ ለመኖርም የሚሳናቸው አልነበሩም። ሆኖም ግን ዘረኞቹ (ህወሃቶች) የሚፈፅሙትን ግፍ ተሸክመው፤ ብኩርናቸውን ሸጠው እና ከሰው ተራ ወርደው ለመኖር ሂሊናቸው አልፈቀደላቸውም። ለሚበላና ለሚጠጣ ከንቱ ነገር ብለው ጥቂት ዘረኞችን ተሸክሞ ከመኖር ይልቅ የነፃነቱን መንገድ መርጠዋልና ጀግኖች ብለን ብናወድሳቸው ተገቢ ይሆናል። እንዲህ ዓይነቱን ውሳኔ የሚወስን ሃሞተ ኮስታራ ጀግና እንጂ ሌላ አይደለም።

አሁንም ለራሳችሁ ክብር ያላችሁና ተመሳሳይ እርምጃ ለመዉሰድ በዝግጅት ላይ የምትገኙ የአገር መከላከያ አባላት እንዳላችሁ እናውቃለን። ቅምጥሎቹ ጄኔራል ተብየዎች ከድሃ ወገኖቻችሁ ላይ የዘረፉትን ዘርፈው አገሪቷን ጥለው መሄድ ጀምረዋል። ቀሪዎችም የዘረፉትን የድሃ ንብረት ወደ ውጪ አገር እያሸሹ እንደሆነም ይታወቃል። በአጠቃላይ በእናንተ ምርኩዝነት አገራችንን እያፈራረሷት፤ ህዝቧንም እያወረዷት ነው። የህዝቡም መከራና እሮሮ ተወርቶ የሚያልቅ አይደለም። እንዲህ አይነቱን ግፍና በደል እያዩ ከንፈር መምጠጥ እያበቃ ነው። እንግዲህ አሁን እኔ ብቻየን ምን አደርጋለሁ የሚባልበት ግዜ እያለፈ ነው። ጋሻ መከታ እና የኋላ ደጀን የሚሆኗችሁ ብዙ አገር ወዳድ ኢትዮጵያዉያን በየቦታው አሉ። ብትወድቁ የሚያነሷችሁ፤ ብትደሙ ደማችሁን የሚያብሱላችሁ፤ ብትሰው መስዋእትነታችሁን ለትውልድ የሚዘክሩላችሁ ወገን አለላችሁ። አትፍሩ። ከዘረኞቹ መንደር ወጥታችሁ የነፃነቱን ትግል እንድትቀላቀሉ ወገናዊ ጥሪያችንን እናቀርብላችኋለን።

ህውሃት ማለት የዘራፊዎች እና የጨካኝ ነፍሰ ገዳዮች ስብስብ መሆኑን ያለምንም ጥርጥር ማመን አለባችሁ።ህወሃት ስንቱን አርዶ፤ ስንቱን ገድሎ፤ ስንቱን አጥፍቶ፤ የስንቱን ኑሮ በትኖ፤ ስንቱን ዘርፎ ባዶ እጁን አስቀርቶ በትረ ስልጣኑን እንደያዘ ምስክር የሚያስፈልገን አይደለም።

የህውሃት ዘረኝነትና ዝሪፊያ የቆጨህ እና ለራስህ ክብር ያለህ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ተነስተህ ትግሉን ተቀላቀል።እነዚህን ግፈኞች የሚፈፅሙትን በደል እያዩ ዝም ማለት ግፉን ከመደገፍ ተለይቶ የሚታይ አይደለም። እናንተ ለራሳችሁ፤ ለወገናችሁና ለአገራቸችሁ ክብር ያላችሁ ዜጎች ዝም በማለታችሁ ህወሃቶች ዝምታችሁን እንደ በጎ ፈቃድ ቆጥረውት የግፍ ሰይፋቸውን ወደ ሰገባው ሊመልሱ ፈቃደኞች አልሆኑም። በማን አለበኝነታቸውም ፀንተው ቆመዋል። እነዚህን ግፈኞች በቃ ለማለት ግዜው ደርሷልና የነፃነቱን ትግል ሳትዘገዩ አሁኑኑ ተቀላቀሉ።

እኛም ወደ ነፃነት ትግሉ እንድትቀላቀሉ ጥሪ ስናደርግላችሁ ለአገራችን ክብርና ለወገኖቻችን በሰላም መኖር ስንል ቆርጠን የተነሳን መሆናችንን ልንገልጽላችሁ እንወዳለን። የግንቦት ሰባት ንቅናቄ በምንም ሁኔታ በዘረኞች እጅ ተንቆና ተዋርዶ መኖርን አይቀበልም።እንዲህ ዓይነቱን ውርደት ተቀብሎ ለመኖር ሰው መሆናችን ይከለክለናል። እነዚህን ዘራፊዎች ተሸክመን ከመኖር ከነፃነታችን ጋር አያቶቻችን በተሰውበት ተራራ ላይ ቆመን መሰዋትን እንመርጣለን። አሁን ተነስተናልና የሚያቆመን የለም። እግዚአብሄርም መንገዳችንን ያከናውንልናል። ኑ ሀገርን ለማዳን የነጻነት ትግሉን ጎራ ተቀላቀሉ።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!**

## አፍንጫ ሲመታ . . . (ከገጽ 4 የዞረ)

ሆነ ፌዴራል ፖሊሰ የኢትዮጵያን ህዝብ ልክ እንደዉጭ ጠላት ሲጨፈጭፉ ነዉ። አግአዚ መግደል ብቸኛ ሙያዉ ነዉና ግደል ተብሎ ሲገድል ይነድደናል ወይ ያሰቆጨናል እንጂ አይገርመንም። የሚገርመን፤ የሚያስቆጨን፤ የሚያንገበግበንና ወያ ነዶ የሚያሰኘን ህዝብን ለመጠበቅ ከህዝብ ዉስጥ ተመልምሎ የሰለጠነዉ ፌዴራል ፖሊስ በወገኖቹ ገንዘብ የተገዛዉን ጠመንጃ እዛዉ ወገኖቹ ላይ ሲያዞር ነዉ።

የ1997ቶቹን ነቢዩ ኃይሌን፤ ጎብታሙ ቶላንና ሽብሬ ደሳለኝን ከሰሞኑ እንደ ቅጠል ከረገፉት ደግሞ ሀቢብ ዋቢን፤ አደም ጀማሎንና ወንድማማቾቹን ገመቹ ተኪንና ታከለዉ ተኪን ስናስብ ኢትዮጵያዊነት በፍጹም ያልጎበኘዉ የፌዴራል ፖሊስ ጭካኔና አረመኔነት ይገርመናልም ያንገበግበናልም። እኛ ኢትዮጵያዉያን የጥንትም ሆነ የዘመኑ ታሪካችን የሚነግረን እህቶቻችን “ወንድም ጋሻ” ድረስ ሲሉን ልማዳችን በፍጥነት ደርሰን እህቶቻችንን መታደግ ነዉ እንጂ የእህቶቻችንን አንገት በጥይት ቀንጥሰን መጣል አይደለም። ታድያ ይህ ትናንት የሽብሬ ደሳለኝን አንገት ቀንጥሶ የጣለዉና ዛሬ ደግሞ ጡት ያልጨረሰች ህጻን ልጅና እናቷን በአንድ ጥይት ያጋደመዉ ፌዴራል ፖሊስ ዬት የበቀለ ትዉልድ ነዉ? ለመሆኑ ፌዴራል ፖሊስ ወገንና ጠላት ለይቶ ለዘረኞችና ለስልጣን ሱሰኞች ሳይሆን ለህገመንግስት የሚገዛ ኃይል ነዉ ወይስ እንደጨበጠዉ ጠመንጃ ግዑዝ የሆነና ተኩስ በተባለ ቁጥር ማንም ላይ የሚተኩስ ተንቀሳቃሽ ሮቦት ነዉ? ከመቼ ወዲህ ነዉ ኢትዮጵያዊ ኃይል በፀረ ኢትዮጵይ ኃይሎች እየተመራ ኢትዮጵያዉያንን በግፍ መግደል የጀመረዉ? ጡት የሚጠባ ህጻን ልጅ እሬሳ በጥይት የተመታች እናቱ ደረት ላይ ተጋድሞ ማየት አንድ ኢትየጵያዊ ዜጋን ቀርቶ ኢትዮጵያዉያንን ሊገድል የመጣ የጠላት ወታደርንም አንጀት የሚበላ እጅግ በጣም አሳዛኝ ክስተት ነዉ። የኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ አባላት ግን በዚህ አይነቱ ዘግናኝ ተግባር የሚያዝኑ መሆናቸዉ ብቻ ሳይሆን እነሱ እራሳቸዉ ናቸዉ ይህንን ሂትለር በአይሁዶች ላይ የፈፀመዉን አይነት ታሪካዊ በደል በወገኖቻችን ላይ የሚፈጽሙት።

ህይወታቸዉን መምራት የሚችሉበት ሌላ አማራጭ አጥተዉ ፌዴራል ፖሊስ የገቡና እንዲሁም የገቡበት ቦታ ጨንቋቸዉና በህዝብ ላይ የሚፈፅሙት ግፍ አንገፍግፏቸዉ መዉጪያ ቀዳዳ የሚፈልጉ አያሌ የፌዴራል ፖሊስ አባላት አሉ። በእኛ ግምትና እምነት መሳሪያ በእጁ የጨበጠ ሰዉ መዉጫና መግቢያ ፈልጎ ማግኘት አያቅተዉምና እነዚህ በፌዴራል ፖሊስ ዉስጥ የሚገኙ አገርና ወገን ወዳድ ኢትዮጵያዉያን የነጻነት ኃይሎችን ለመቀላቀል ከአሁን የተሻለ ግዜና አጋጣሚ የሚያገኙ አይመስለንም፤ ስለሆነም በግልም ሆነ በነጠላ እራሳቸዉን እያደራጁ የነጻነት ኃይሎችን እንዲቀላቀሉ እያሳሰብን የኢትዮጵያን ትንሳኤ በማፋጠን የበደሉትን ህዝብ እንዲክሱ አገራዊ ጥሪ እናቀርብላቸዋለን። ይህንን ጥሪ የማይቀበልና በተለይ ከወያኔ ዘረኛ አገዛዝ የሚሰጠዉን የግደል ጥሪ እተቀበለ የገዛ ወገኖቹን የሚገድል የፌዴራል ፖሊስ አባል ይህ የበሰበሰ ስርዐት መዉደቂያዉ ሩቅ አይደለምና ከህዝብ ቁጣና ፍርድ እንደማያመልጥ ደግመን ደጋግመን ልናሳስብ እንወዳለን።

## ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ በፖሊስ ታስረዉ ተፈቱ

የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ሊቀመንበርና የቀድሞዉ የኢትዮጵያ ፕሬዘዳንት ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ባለፈዉ ረቡዕ መስከረም 15 ቀን ለግማሽ ቀን ያክል ታስረዉ መፈታታቸዉን አዲስ አበባ ዉስጥ የሚገኙ የግንቦት ሰባት ድምጽ ዘጋቢዎች ገለጹ። ዶ/ር ነጋሶ የታሰሩት የፊታችን እሁድ መስከረም 19 ቀን የአንድነት ፓርቲ በአዲስ አበባ መስቀል አደባባይ ለጠራው ህዝባዊ የተቃውሞ ሰልፍ ቅስቀሳ ለማድረግ ወደ ሽሮ ሜዳ የተሰማራዉ ቡድን አባላት መታሰራቸዉን ሰምተዉ ወደ ታሰሩበት ቦታ በመሄድ እነሱን ያዘዝኳቸዉ እኔ ሰለሆንኩ እነሱን ፍቱና እኔን እሰሩ በማለታቸው የጣቢያው ፖሊሶች እንዳሰሯቸዉ ለማወቅ ተችሏል። ከዚህ በተጨማሪ ዶ/ር ነጋሶ ልጆቹ የፈጸሙት ህገ ወጥ ድርጊት የለም፣ሲቀሰቅሱ የነበሩትም መንግስት ፈቃድና እውቅና ለተሰጠው ሰላማዊ ሰልፍ ነው ብለዉ መናገራቸዉ ታዉቋል። ይህ በእንዲህ አንዳለ በዶ/ር ነጋሶ ሲታሰሩ የተለቀቁት የአንድነት ፓርቲ አባላት ቅስቀሳቸውን በመቀጠል ህዝቡ በመጪዉ እሁድ በነቂስ ወጥቶ ተቃዉሞዉን እንዲያሰማ ጠይቀዋል። በሌላ በኩል ለእሁዱ ሰልፍ በቄራ አካባቢ ቅስቀሳ ሲያደርጹ የነበሩ የአንድነት አባላት ሲታሰሩ ለቅሰቀሳ ይጠቀሙበት የነበረዉ መኪናም በፖሊሶች መታገቱ ታዉቋል።

## አፍንጫ ሲመታ የማያለቅስ አይን - አይን አይደለም

የአዉሮፓን ቅኝ ገዢዎች ጀርባና ፊት በአይኑ በፍጹም ያላየ የአፍሪካ ህዝብ ቢኖር የኢትዮጵያ ህዝብ ብቻ ነዉ። አዎ! ኢትዮጵያ በቅኝ ገዢዎች ያልተገዛች አገር ብቻ ሳትሆን በቅኝ ገዢዎች ላይ አኩሪና አንጸባሪቂ ድል የተዳጀች የአለማችን ብቸኛ የጥቁር ህዝብ አገር ናት። የኢትዮጵያ ህዝብ በቅኝ ገዢዎች ያልተገዛዉ ቅኝ ገዢዎች ስላላዩት ወይም ኢትዮጵያ የግዜዉን ቅኝ ገዢዎች የማታጓጓ አገር ሆና አይደለም። አዉሮፓዉያን ወይም ቅጥረኞቻቸዉ የኢትዮጵያን ህዝብ አንበርክከዉ አገሩን መያዝ ያልቻሉት ኢትዮጵያ ዳር ድንበሯ ሲደፈር እያዩ እቤታቸዉ ተኝተዉ የሚያድሩ ልጆች ሰለሌሏት ነዉ። የኢትዮጵያ ህዝብ ጀግኖች ልጆቹ በከፈሉት መስዋዕትነት የፖለቲካ ነጻነቱን ሳያስደፍር በሺዎች ለሚቆጠሩ አመታት የኖር ቢሆንም የአገር ዉስጥ አምባገነኖች ግን ለብዙ ዘመናት ቁም ስቅሉን ያሳዩት ህዝብ ነዉ።በተለይ የዛሬዎቹ ዘረኛ አምባገነኖች ከዉጭ ቅኝ ገዢዎች ባልተለየ መንገድ የኢትዮጵያን ህዝብ ሰብዓዊ መብቶች ረግጠዋል። የጣሊያን፤ የእንግሊዝና የፈረንሳይ ቅኝ ገዢዎች ቅኝ በገዟቸዉ አገሮች እንዳደረጉት ሁሉ የዛሬዎቹ የአገር ዉስጥ ቅኝ ገዢዎች የኢትዮጵያን ህዝብ ረግጠዉ መግዛት እንዲችሉ ህዝቡን በሐይማኖት፤ በዘርና በቋንቋ ከፋፍለዋል። የአዉሮፓ ቅኝ ገዢዎች የአገር ዉስጥ ከሀዲዎችን መልምለዉ መናኛና ጥርስ የሌለዉ ሹመት እየሰጡ አገሬዉ ጸጥ ለጥ ብሎ እንዲገዛላቸዉ አድርገዋል፤ የወያኔ አገዛዝም ይህንን መሰሪ የቅኝ ገዢዎች አሰራር አንዳለ ኮፒ በማድረግ ኦጋዴን፤አፋር፤ ኦሮሚያ፤አማራ፤ጋምቤላ፤ ቤንሻንጉልና ደቡብ ክልል ዉስጥ በራሳቸዉ አምሳል የክልል ምስለኔዎችን ፈጥረዉ ህዝብ አጎንብሶ እንዲገዛላቸዉ አድርገዋል።

አዉሮፓዉያን ቅኝ በገዟቸዉ አገሮች ዉስጥ ሁሉ የህዝብን ቅስም ሰብረዉ የሦስተኛዉን አለም ህዝቦች አንበርክከዉ በቅኝ ገዢነት ለብዙ አመታት እንዲቀጥሉ ያስቻለቸዉን ከፍተኛ ሠራዊትና ሰላይ ያገኙት ከዚያዉ ቅኝ ከሚገዙት ህዝብ መኃል ነዉ እንጂ ከአዉሮፓ ይዘዉ የሄዱት ሠራዊት እጅግ በጣም ትንሽ ነዉ። በአምስት አመቱ የጣሊያን ወረራ ግዜ መረጃ በማቀበል በተዋጊነትና የጣሊያን ፋሺስቶችን መልካምነት በመናገር የኢትዮጵያ አርበኞችን ትግል እጅግ በጣም አድካሚ ያደረጉት ኢትዮጵያዉያን ባንዳዎች እንደነበሩ የታሪክ ማህደራችን በግልጽ ይናገራል። ኢትዮጵያ በህይወታቸዉ ቆርጠዉ ጣልያን ጓዳ ድረስ ዘልቀዉ ገብተዉ አገርን ከዉድቀት ትዉልድን ደግሞ ከዉርደት ያዳኑ ባሻ አዉዓሎምንና ሸዋረገድ ሐይሌን የመሳሰሉ ጀግኖች እንደነበሯት ሁሉ ኢትዮጵያን በሻንጣ ጠቅልለዉ ለጣልያን ለማቀበል ብዙ የደከሙ የባንዳዎቹ የነ ኃይለሥላሤ ጉግሳም አገር ናት።

ባለፉት አምስት አመታት ግንቦት ሰባት የፍትህ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ለህዘብ ይፋ ባደረገዉ የተለያዩ በቁጥር የተደገፉ መረጃዎች መሠረት ወያኔ አይወክልም አንጂ እወክላለሁ ብሎ የሚናገረዉ ወይም የወያኔ የፖለቲካ ኃይል ምንጩ የትግራይ ክልል ነዉ። የትግራይ ክልል ህዝብ ደግሞ ብዛቱ ከ4.5 ሚሊዮን ብዙም አይበልጥም። ታድያ እንዴት ሆኖ ነዉ ከዚህ ከአገራችን ህዝብ ብዛት 6 በመቶ ብቻ ከሆነዉ ከትግራይ ክልል የመጡ ጥቂት የፖለቲካ ሊ‚ቃቂቶች 94 በመቶ የሚሆነዉን የኢትዮጵያ ህዘብ እጅና አግር አስረዉ እየቀጠቀጡ መግዛት የቻሉት? እንዴት ሆኖ ነዉ የእነዚህ ጥቂት ከሃዲዎች ቡድን በፖሊስ፤ በድህንነት፤ በጦር ኃይሎች፤በኤኮኖሚና በሌሎችም የተለያዩ ዘርፎች ዉስጥ የራሴ የሚላቸዉን ሰዎች አስቀምጦ አገራችንን እንዳሰኘዉ ማድረግ የቻለዉ? መለሱ ቀላል ነዉ። ኢትዮጵያ ትናንት እንደነበሩባት ሁሉ ዛሬም ኃ/ሥላሤ ጉግሳና መሰል ጓደኞቹ አሏት። አዎ! ትናንት የነጭ ፋሺችቶችን ጠመንጃ ተሸክመዉ የገዛ ህዝባቸዉን ደም እንደ ጎርፍ ያፈሰሱ ባንዳዎች፤ እራስ ወዳዶችና የአዕምሮ እዉራን እንደነበሩን ሁሉ ዛሬም የጥቁር ፋሺስቶችን ጠመንጃ ተሸክመዉ የራሳቸዉን ወገኖች ካለ ርህራሄ የሚጨፈጭፉ ጨካኝና አረመኔ ኃይሎች አሉ። ከእነዚህ ከህዝብ አብራክ ወጥተዉ የተሰጣቸዉን ጠመንጃ ቃታ ከመሳብ ዉጭ ሌላ ምንም ህዝባዊ አደራና አገራዊ ስሜት ከማይሰማቸዉ ጨካኝና ግዑዝ ኃይሎች ዉስጥ አንዱና ዋነኛዉ ፌዴራል ፖሊስ በመባል የሚታወቀዉ ስብስብ ነዉ።

ፌዴራል ፖሊስ ወያኔ አዲስ አበባ ገብቶ አብሮ በኖረ ህዝብ መኃል የዘርና የጎሳ አጥር ከሰራ በኋላ የከፋቱ ማራመጃና የተንኮል ዕቅዱ ማስፈጸሚያ እንዲሆነዉ ከፈጠራቸዉ ተቋሞች ዉስጥ አንዱ ነዉ። ፌዴራል ፖሊስ አመሰራረቱም ሆነ የቀን ከቀን ስራዉ ከኢትዮጵያ ህዝብ ጥቅምና ፈላጎት ጋር በምንም መልኩ የተገናኘ አይደለም። ፌዴራል ፖሊስን የፈጠረዉ ወያኔ፤ የሚመራዉና የሚቆጣጠረዉ ወያኔ፤ ፌዴራል ፖሊስ በሚወስዳቸዉ ጸረ ህዝብ እርምጃዎች ዋነኛዉ ተጠቃሚም ወያኔ ብቻ ነዉ።የፌዴራል ፖሊስ ከተቋቋመበት ግዜ ጀምሮ የወሰዳቸዉን ጸረ ህዘብና ጸረ አገር እርምጃዎች አንድ በአንድ ስንመለከት ይህ ተቋም በሚወስዳቸዉ እርምጃዎች የሚጎዳዉ የገፈቱ ቀማሽ የሆነዉ የኢትዮጵያ ህዝብ ብቻ ሳይሆን የፌዴራል ፖሊስ አባላት እራሳቸዉም ቢሆኑ በግልና በቡድን የራሳቸዉ እርምጃ ሰለባዎች ናቸዉ። ታድያ ለምንድነዉ ፌዴራል ፖሊስ ከ20 አመት በላይ እሱን እራሱንና እናቱን፤ አባቱን፤ እህቱንና ወንድሙን የሚጎዳ እርምጃ የሚወስደዉ? የታጠቀ ኃይል ማለትም ፖሊስ፤መከላከያ ሠራዊትና ህዝባዊ ሚሊሺያ ለአዛዦቻቸዉ መታዘዝ እንዳለባቸዉ ከማንም የተሰወረ አይደለም፤ ሆኖም መታዘዝ አንዱ ሀቅ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ትዕዛዝ ሰጪዉ ወያኔ በጥላቻና በዘረኝነት የተነከረ ኃይል ነዉ። ታድያ የወያኔ ጥላቻና ዘረኝነት ጧትና ማታ የሚፈራረቁበት ፌዴራል ፖሊስ እነዚህ ዘረኞች ሂድና ወገኖችህን ግደል ብለዉ ሲያዙት ለምንድነዉ ትዕዛዛቸዉን አልቀበልም የማይለዉ?

ለመሆኑ ይህ ወያኔ ሰራሽ የሆነዉ ፌዴራል ፖሊስ የፊዉዳል ኃ/ሥላሤን ስርዐት ለመደምሰስ በተካሄደዉ ትግል ዉስጥ በፊዉዳሉ ስርዐት መቃብር ላይ የመጨረሻዉን ችንካር የቸነከሩት የፖሊስ ሠራዊት፤ የጦር ኃይሎችና የብሔራዊ ጦር አባላት መሆናቸዉን ያዉቃል? ደርግን ለመጣል በተደረገዉ የሞትና የሽረት ትግል ዉስጥም ቢሆን መሳሪያ የታጠቁ አማጽያንን እየሄዱ በመቀላቀል ደርግን የተዋጉት ደርግ እራሱ ያሰለጠናቸዉ የፖሊስ ሰራዊትና የመከላከያ ሠራዊት አባላት መሆናቸዉንስ ያዉቁ ኖሯል? ታድያ ምነዉ የዛሬዎቹ ፌዴራል ፖሊስና የመከላከያ ሰራዊት አባላት እያረረ የሚስቅ ማሽላ ሆኑ? እዚህ ላይ ወያኔ በየክልሉ ህዝብን እንዲገድሉ ያሰማራቸዉን የፌዴራል ፖሊስ አባላት አንድ የምንጠይቃቸዉ ጥያቄ አለ፤ እሱም በታጠቁት መሳሪያ በነጋ በጠባ የሚገድሉት ህዝብን ከሆነ ከአደጋና ከጥቃት የሚጠብቁትስ ማንን ነዉ?

በ2011 ዓም ጣሂሪር አደባባይ ላይ የተሰበሰበዉ የግብፅ ህዝብ ላይ የሙባረክን ትዕዛዝ ተከትሎ የግብፅ ጦር እርምጃ ወስዶ ቢሆን ኖሮ ዛሬ የአረቡ አለም አብዮት ተብሎ የሚጠራዉና ከ150 ሚሊዮን በላይ አረቦችን ከአምባገነኖች ያላቀቀዉ ትልቁ የዘመናችን ክስተት እንደተራ ነገር ተረስቶ ይቀር ነበር። አስተዋዩ የግብፅ ጦር ግን መኃላዉ ለሙባረክ ሳይሆን ለህዝብና ለአገር መሆኑን ስለሚረዳ በዚያ ክፉ ቀን ሙባረክን ከድቶ ከህዝብ ጋር ቆመ። በነገራችን ላይ የኢትዮጵያ ህዝብ ዘረኝነትንና አምባገነንነትን አሽቀንጥሮ ጥሎ ነጻነቱን እንዳያዉጅ ደንቃራ ሆነዉ ያስቸገሩት ግደሉ ሲባሉ ተሽቀዳድመዉ የሚሄዱት የአግአዚ አባላት ብቻ ሳይሆኑ ከኢትዮጵያ ግፉዓን አብራክ የወጣዉ የፌዴራል ፖሊስ አባላት ጭምር ናቸዉ። ይህ የሚያሳየን ደግሞ የፌዴራል ፖሊስ አባላት የሚገድሉት የኢትዮጵያን ህዝብ ብቻ ሳይሆን የነገ ተስፋዉን ጭምር መሆኑን ነዉ።

ወታደራዊ ትዕዛዝ መቀበል አንድ ነገር ነዉ፤ የዘረኞችን ትዕዛዝ ተቀብሎ በነጋ በጠባ የንጹሀን ዜጎችን ደም ማፍሰስ ግን ሂሊና ካለዉ ከማንም ሰዉ የሚጠበቅ ተግባር አይደለም። የኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስም ቢሆን አንዴ፤ ሁለቴ፤ ወይም ሦስቴ የበላዮቹን ትዕዛዝ ተቀብሎ ህዝብን የሚጎዳ እርምጃ ይወስድ ይሆናል ግን ፌዴራል ፖሊስ ምን አይነት ጨካኞች የተሰበሰቡበት ስብስብ ቢሆን ነዉ እሱን እራሱንና ወገኖቹን በዘር፤ በቋንቋና በሐይማኖት ከፋፍሎ እንደ እንሰሳ እየረገጠ የሚገዛን ኃይል እየታዘዘ ሃያ አመት ሙሉ ወንድሞቹንና አህቶቹን የሚገድለዉ? የወያኔ ዘረኞች መሳሪያ አስታጥቀዉ እንዲጠብቃቸዉ ያሰለጠኑትንም ኃይል ቢሆን በዘርና በቋንቋ ከፋፍለዉ ነዉ የሚገዙት፤ ወያኔ በፌዴራል ፖሊስ፤ በመከላከያ ሰራዊትም ሆነ በደህንነት ዉስጥ ከትግርኛ ተናጋሪዎች ዉጭ የአዛዥነቱን ቦታ ሌላ ለማንም እንደማይሰጥ በግልጽ ይታወቃል። ታድያ ፌዴራል ፖሊስ መቼ ይሆን ከዚህ የቀን መኝታዉ ነቅቶ ሌላ ቢቀር የራሱን መብት፤ ነጻነትና እኩልነት የሚያስከብረዉ? መቼ ነዉ ፌዴራል ፖሊስ የታጠቀዉን መሳሪያ ወገኖቹ ላይ ሳይሆን ወደ ዘረኞችና ወደ ህዝብ ጠላቶች ላይ የሚያዞረዉ?

የኢትዮጵያ ህዝብ ሰኔ 1997ና ህዳር 1998 ዓም አግአዚና ፌዴራል ፖሊስ ተጋግዘዉ ያደረሱበትን በደል አሁንም አልረሳዉም። አግአዚ ኢትዮጵያዉያንን ለመግደል ሆን ተብሎ የተቋቋመ ኃይል ነዉና ግደል ሲባል ጥያቄዉ “ለምን ልግደል” ሳይሆን ስንት ልግደል ነዉ፤ ከዚህ በተጨማሪ አግዓዚ እሱ ከሚናገረዉ ቋንቋ ዉጭ የሚናገሩ ኢትዮጵያዉያንን በመግደል የሚደሰት በጭራቅ የሚመሰል ጦር ነዉ። አዛዦቹም እንደዚሁ ልክ እንደነሱ ትግርኛ የማይናገር ኢትዮጵያዊ ሞት ሞትም አይመስላቸዉም። ለዚህ ነዉ እነሱ ከሚያስቡት ዉጭ የተለየ አስተሳሰብ ያለዉን ኢትዮጵያዊ ሁሉ እሰሩ፤ደብድቡ ወይም ግደሉ እያሉ የሚያዝዙት። ታድያ የትግራይ ክልልን ጨምሮ ከተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች ተመልምሎ የመጣዉ ፌዴራል ፖሊስ ምን አይነት ጭካኔ ቢያስተምሩት ነዉ መብቴን አክብሩልኝ ብሎ ሰላማዊ ሠልፍ የወጣዉን የራሱን ወገን ልክ እንደ ጦር ሜዳ ጠላት ደረት ደረቱን በጥይት እየመታ የሚገድለዉ? በተለይ ፌዴራል ፖሊስ ባለፈዉ በሐምሌ ወር ማለቂያ አካባቢ በኮፈሌና በአካባበቢዋ የማምለክ መብቴ ይከበርልኝ ብሎ የጠየቀን ህዝብ መኖሪያ አካባቢዉ ድረስ በመሄድ በግፍ የጨፈጨፈዉ ለምንድነዉ? ለመሆኑ ፌዴራል ፖሊስ በሱና ሆነ በወገኖቹ ላይ የሚፈጸመዉ ግፍና በደል ተሰምቶት ከወገኖቹ ጎን የሚቆመዉ መቼ ይሆን?

አግዓዚ ጦር የተቋቋመዉም የሚኖረዉም የወያኔን ስልጣንና ክብር ዘለአለማዊ ለማድረግ ነዉ። ፌደዴራል ፖሊስ ግን ሌላ ቢቀር ስሙ ፌዴራል ነዉና ተቀዳሚ ተግበሩ መሆን ያለበት በፌዴራል ኢትዮጵያ ድንበር ዉስጥ የሚኖረዉ ህዝብ ዘሩና ቋንቋዉ ሳይለይ መብቱ፤ ነጻነቱና እኩልነቱ ተከብሮ እንዲኖር ማድረግ ነዉ። ዛሬ በተግባር የምናየዉ ግን አግአዚ ጦርም (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ጋዜጠኛ ብስራት ወ/ሚካኤል በወያኔ ደህንነቶች ታግቶ መደብደቡ ከወደ አዲስ አበባ ተሰማ

ታዋቂዉ ኢትዮጵያዊ ጋዜጠኛ ብስራት ወ/ሚካኤል በወያኔ የደህንነት ኃይሎች ታግቶ እንደተደበደበና የአካልና የስነልቦና ጉዳትም እንደደረሰበት ከአዲስ አበባ ለዝግጅት ክፍላችን የደረሱን ዜናዎች ያስረዳሉ። ጋዜጠኛ ብስራት ይህ ኢትዮጵያ ዉስጥ ሀቅን በሚጽፉና በሚናገሩ ጋዜጠኞች ላይ ሁሌም የሚደርሰዉ ችግር የደረሰበት ባለፈዉ ነኃሴ 28 ቀን ጎተራ አካባቢ ወደ መኖሪያ ቤቱ ሲሄድ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል። ከአዲስ አበባ የደረሰን ዜና ጨምሮ እንደሚያስረዳዉ ጋዜጠኛ ብስራት ከዚህ አስር፤ እንግልትና ድብደባ የበቃዉ በህገ መንግስቱ የተረጋገጠለትን ሀሳብን በንግግርና በጽሁፍ የመግለጽ መብቱን ስለተጠቀመ እንጂ ሌላ በወንጀል የሚያስጠይቅ ምንም ስራ እንዳልሰራ ታዉቋል። ሁኔታዉን እንደ ተከታተሉ የፖለቲካ ተንታኞች አባባል ጋዜጣኛዉ ወንጀል ቢሰራ እንኳን ፖሊሰ የፍርድ ቤት ፈቃድ ካገኘ በኋላ ተጠርጣሪዉን በቁጥጥር ስር አዉሎ ለፍርድ ያቀርባል እንጂ መደብደብና ማጎሳቆል አይችልም።

ጋዜጠኛ ብስራት ኢቦኒ የሚባል አገር ዉስጥ የሚታተም መጽሄት ዋና አዘጋጅ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ ለተለያዩ መጽሄቶች፤ ድረገጾችና ብሎጎች የፖለቲካ ይዘት ያላቸዉን መጣጥፎች የሚጽፍ ወጣት ጋዜጠኛ ነዉ። የጋዜጠኛ ብስራት ጽሁፎች በአብዛኛዉ የሚያተኩሩት በወያኔ አገዛዝ አስተዳደራዊ ብልሹነትና በአገዛዙ የሰብዓዊ መብትና ነጻነት ረገጣ ጉዳይ ላይ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል። እንደብዙ አስተያየት ሰጪዎች ግምት የገዢዉን ፓርቲ አባላት ያስቆጣዉና ጋዜጠኛዉን ለእስርና ለእንግልት ያበቃዉ ይሄዉ በአገዛዙ ላይ በረደጋጋሚ የሚሰነዝራቸዉ ትችቶች ናቸዉ። ጋዜጠኛ ብስራት እንዴት እንደታሰረ በዝርዝር ሲያስረዳ ሐምሌ 28 ቀን 2005 ዓም ከጥዋቱ ሦስት ሰአት ተኩል አካባቢ ከስራዉ ወጥቶ ወደ ቤቱ ሲሄድ አራት ሲቪል የለበሱ ድህንነት አባላት የሚሄድበት መንገድ ላይ መጥተዉ ለጥያቄ እንደልግህለን ብለዉ እኢደወሰዱትና በተለይ አንደኛዉ የደህንነት አባል የስለት መሳሪያ አዉጥቶ ሆዱ ላይ ደቅኖበት እያስፈራራዉ ከመንገድ አስወጥቶ ወደ ጨለማ ቦታ እንደወሰዱት ተናግሯል። ከዚያም እየጎሻሸሙ አንተ ማነህ ስለ መለስ ዜናዊ የምትጽፈዉ? ስለ መለስ ዜናዊ ኃብትስ ምን አገባህና ነዉ የምትጽፈዉ፤ ህይወትህን የምትፈልጋት ከሆነ ከዛሬ በኋላ መጻፍህንና እየጻፍክ በየድረገጹ መላክህን አቁም - ይህ የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ነዉ ብለዉ እንዳስፈራሩት ጋዜጠኛ ብስራት ለጋዜጠኞች በሰጠዉ መግለጫ ተናግሯል። ጋዜጠኛ ብስራት በዕለቱ የደረሰበትን በደልና እንግልት በአካባቢዉ ለሚገኘዉ ፖሊስ ጣቢያ ሄዶ ሪፖርት ያቀረበ ቢሆንም ሪፖርቱን አጣጥሎ የተመለከተዉ ፖሊስ ጣቢያ ጉዳዩን ተቀብሎ ለመመዝገብ ከሁለት ቀን በላይ እንደወሰደበት ታዉቋል።

## ደጃች ዉቤ ሠፈር ሊፈርስ መሆኑ ተነገረ

ኢትዮጵያንና ታሪኳን ጨርሶ ሳያጠፋ እንቅልፍ ባይኑ አልዞር ያለዉ ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ ከአዲስ አበባ ከተማ ምስረታ ጋር አብሮ የተቆረቆረዉን በተለምዶ "ዉቤ በረሃ" በሚል መጠሪያ የሚታወቀዉን ታሪካዊዉን ደጃች ዉቤ ሠፈር ለማፍረስና በራሱ አምሳያ እንደገና ሊፈጥረዉ በዝግጅት ላይ መሆኑን ጉዳዩ ያሳሰባቸዉ የክፍለከተማዉ ነዋሪዎችና አገር ወዳድ ግለሰቦች አጋለጡ። በአራዳ ክፍለ ከተማ ከጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት ወደ አፍንጮ በር በሚወስደው መንገድ በቀኝ በኩል ባለዉ ሰፋ ያለ ቦታ የሚኖሩ እንደሚነሱና ይህ ከ100 ዓመታት በላይ ያስቆጠረው ታሪካዊ ሠፈር እንደሚፈርስ ለነዋሪዎቹ የተነገራቸው በያዝነዉ መስከረም በሀገር ፍቅር ቴአትር በተደረገ ውይይት እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል። ይህ አስደንጋጭ ዜና የደረሳቸዉ ከራስ መኮንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በሚወስደዉ መንገድ ላይ የሚገኙ መኖሪያ ቤቶች፣ የንግድ ቤቶች፤ የተለያዩ ቢሮዎች፣ ሆቴሎችና ምግብ ቤቶች ባለቤቶች ጉዳዩ በጣም እንዳሳሰባቸዉ ከመናገራቸዉም በላይ ከነሱ መፈናቀል በላይ ያሰሰባቸዉ ይህ ከአዲስ አበባ ከተማ ምሥረታ ጋር ተያይዞ በቀደምትነት የተመሰረተዉ ታሪካዊ ቦታ እንዲህ እንደዋዛ ይፍረስ መባሉ አንደሆነ በምሬት ተናግዋል።

ታሪካዊዉን የደጃች ዉቤን ሰፈር ለማፍረስ የተፈለገዉ የባቡር ተርሚናልና ኃይል መስጫ ጣቢያ ለመገንባት ነዉ ያሉት ሰፈሩ ነዋሪዎች ደርግ እንኳን ነዋሪዎችን ሲያፈናቅል ሕንፃ ገንብቶ በማስረከብ እንደነበር የሚናገሩት ነዋሪዎቹ ወያኔ ግን "ምን ያመጣሉ" በሚል ንቀት በማለት ለዘመናት የኖሩበት ቤት ግማሽ አመት በማይሞላ ግዜ ዉስጥ ለቅቃችሁ ዉጡ ማለቱ እንዳስደነገጣቸዉ ተናግረዋል። በአገር ቅርስነቱ እንክብካቤ ተደርጎለት መኖር የሚገባዉ ይህ ታሪካዊ ቦታ እንዲፈርስ መደረጉ ወያኔ ለኢትዮጵያ ህዝብ፤ ታሪክና ቅርስ ግድ እንደሌላዉ በግልጽ ያሳያል ብለዋል። የአራዳ ክፍለ ከተማ የመሬት ልማት ማኔጅመንት ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ግርማ ሙሉጌታ እንደተናገዉ መንግሥት ማንንም መጉዳትና መበደል አይፈልግም ወይም መንግሥት ድርጊቱን እየፈጸመ ያለው ቅርስን ካለመፈለግና ነዋሪዎችን ለማፈናቀል ብሎም አይደለም፤ ሆኖም ቅርስም ሆነ ሌላ ነገር ከባቡር ተርሚናሉ ጋር የሚገናኝ ከሆነ መፍረሱ የማይቀር ነዉ ብሏል።

በደጃች ውቤ (ውቤ በረሃ) ሠፈር ከሚፈርሱት ቤቶች መካከል የኢትዮጵያ ባለውለታ የነበሩትና በዳግማዊ ምኒልክ ዘመን ከቱርክ መሣሪያ በመግዛት ለኢትዮጵያ ያመጡ የነበሩት አርመናዊው ሚስተር ቴራዚያን ቤተሰቦች መኖሪያ ቤት፣ የአፈ ንጉሥ ተክሌ ቤት፣ ከራስ መኮንን ድልድይ በስተቀኝ በኩል የሚገኘው ዓድዋ ሆስቴል፣ የታዋቂው አኮርዲዮን ተጨዋች አቶ ፍሬው ኃይሉ ቤት፤የጄነራል መልኬ ቤት፣ የመጀመሪያው ስፖርት ቤት መሥራች ሙሉ ስፖርት ቤት፣ የመጀመሪያው የቅዱስ ጊዮርጊስ ክለብ በረኛ አቶ ታደሰ ጌጤ ቤት፣ የቡድኑ መሥራችና ተጨዋች የነበሩት አቶ አየለ አትናሽ ቤት ይገኙበታል።

## ግንቦት 7 ዋሽንግተን ዲሲ . . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ሳይሆን የአገራችንን አንድነትና ሰላም አደጋ ላይ ጥለዋል ከሚባሉ ኃይሎች ጋር ነዉ እንጂ ከወዳጅ ጋርማ አብሮ መምከርና መስራት ነዉ እንጂ ድርድር አያስፈልግም ብለዋል።

በዕለቱ ስብሰባ ላይ ሰፋ ያለ መረጃ ለስብሰባዉ ተካፋዮች ያቀረቡት አቶ አንዳርጋቸዉ ጽጌ ሲሆኑ እሳቸዉም በበኩላቸዉ ወያኔን ለማስወገድ የሚደረገዉ ትግል በአሁኑ የአገራችንና የአካባቢያችን ተጨባጭ ሁኔታ መሰረት የግድ ከኤርትራ መንግስት ጋር አብሮ መስራትንና ትብብር መፍጠርን የሚጠይቅ ጉዳይ ነዉ ብለዋል። ግንቦት ሰባትና ኤርትራ ዉስጥ የሚገኙ የተለያዩ ለኢትዮጵያ ህዝብ ነጻነት የሚታገሉ ኃይሎች መስከ ላይ የሚያደርጉትን የትግል ትብብር በምስል አስደግፈዉ የተናገሩት አቶ አንዳርጋቸዉ ጽጌ መለስ ዜናዊ ትግራይ ዉስጥ አጥፍቼዋለሁ ብሎ ይፎክር የነበረዉ የኢትዮጵያዊነት መንፈስ አለመጥፋቱንና ጭራሽ እያበበ መሆኑን ተናግረዋል። ኤርትራ ዉስጥ ካሉ ህዝባዊ ኃይሎች ጋር በተለይ ከትግራይ ህዝብ ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ ጋር እየተደረገ ያለዉ የመስክ ላይ ትብብር በቅርብ ግዜ ዉስጥ ከወያኔ ጋር የሚደረገዉን ትንንቅ ወደ ሌላ ምዕራፍ ይወስዳዋል ብለዉ እንደሚያምኑ ተናግረዋል። ወያኔ አሁን ድረስ ተዝናንቶ የሚገዛን በራሱ ጥንካሬ ሳይሆን በኛ በራሳችን ድክመት ነዉ ያሉት አቶ አንዳርጋቸዉ ጽጌ አዉሮፓና አሜሪካ ዉስጥ የሚገኘዉ ኢትዮጵያዊ እርስ በርስ መናቆሩን ትቶ መሳሪያ ካነሳዉ ኃይል ትምህርት በመቅሰም ህብረት ፈጥሮ የወያኔን እድሜ እንዲያሳጥር ጠይቀዋል።

ለስብሰባዉ ተካፋዮች የግንቦት ሰባትን አንኳር አላማና ግብ ባጭሩ ያሰቀመጡት

ዶ/ር ብርሀኑ ነጋ የግንቦት ሰባት ብቸኛ አላማ ወያኔን ማስወገድና አገሪቱ ወደ ትክክለኛ ዲሞክራሲያዊ ስርዐት ሽግግር እንድታደርግ መርዳት ነዉ ካሉ በኋላ ንቅናቄዉ ይህንን አላማዉን ከግብ ለማድረስ የሚረዳ ድፕሎማሲያዊ ጥረቶችን ያደርጋል እንጂ በፕሮግራም ደረጃ የሚያራምደዉ የዉጭ ግኑኝነት ፖሊሲ የለዉም ብለዋል። ከዚህ በተጨማሪ ዶ/ር ብርሀኑ ግንቦት 7 ከዚህ ቀደምም፤ አሁንም ሆነ ወደፊት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅሞች ላይ በምንም መልኩ አይደራደርም ለመደራደርም ሙከራ አያደርግም ብለዋል። የአሰብን ወደብ ለመመለስ ትታገላላችሁ ወይ ተብሎ ለተጠየቁት ጥያቄ ዶ/ር ብርሀኑ ሲመልሱ ግንቦት ሰባት የተቋቋመበት ዋና አላማ ኢትዮጵያ ዉስጥ ወያኔ ተደምስሶ የፍትህና የዲሞክራሲ ስርዐት እንዲመሰረት ማድረግ ነዉና ይህንን አላማችንን ተግባራዊ ለማድረግ የማንፈነቅለዉ ድንጋይ አይኖርም ካሉ በኋላ ይንን የተነሳንለትን አላማ የሚያለሰልሱና ክንዳችንን ወደ ተለያዩ አቅጣጫዎች እንድንሰነዝር የሚያደርጉንን ሌላ የጎን ስራዎች አቅሙ ስለሌለንና ትኩረታችንንም ስለሚያላሉት አንሰራምም አንሞክርምም ብለዋል።

በመጨረሻም አዳራራሹ ዉስጥ የተገኘዉ ህዝብ እንዴት እንርዳችሁ ብሎ የጠየቀዉን ጥያቄ ሲመልሱ ግንቦት ሰባትንና ህዝባዊ ኃይሉን መርዳት የሚፈልግ ማንኛዉም ኢትዮጵያዊ የሁለቱን ድርጅቶች ድረገጽ በመጎብኘት መረጃ ማግኘት ይችላል ካሉ በኋላ ግንቦት ሰባት የተቋቋመበትን ዋነኛ አላማ ማለትም ወያኔን የማስወገዱን ተግባራዊ እንቅስቃሴ ሲጀምር ያኔ ከህዝብ ጋር እንደሚመክርና እርዳታም እንደሚጠይቅ ተናግረዋል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

መካከኛ ሞገድ:- በ 358 MB, በ 837 kHz
አጭር ሞገድ:- በ 31 MB በ 9700 KHz
በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz
በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org